# ለፍትሕ ሚኒስቴር ለምርመራ የሚላኩ የረቂቅ ሕጎች አቀራረብ እና ምርመራ ሥርዓት መመሪያ

የሚወጡ ሕጎች ተግባራዊ የሚሆኑት በሰዎች ላይ በመሆኑ ከመውጣታቸው በፊት ተገቢውን የሕግ አረቃቀቅ ዘዴዎችን እና ሂደቶችን ተከትለው የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ ሥርዓቶች አንዱ በመሆኑ እና ለዚህም የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሕጎችን ጥራት በማረጋገጥ የወጡበትን ዓላማ በአግባቡ ማሳካት እንዲችሉ እና አፈፃፀማቸውም ውጤታማ እንዲሆን ለምርመራ ለፍትሕ ሚኒስቴር የሚላኩ ረቂቅ ሕጎችን ወጥነት ባለው እና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለመመርመር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢፌዲሪ ፍትሕ ሚኒስቴር በመንግሥት ተቋማት የሚዘጋጁ ረቂቅ ሕጎች የሕግ ማርቀቅ መርሆዎችን የተከተሉ እና ከሕገ-መንግሥቱ፣ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ከሌሎች በሥራ ላይ ካሉ ሕጎች፣ ከሕግ ሥርዓቱ እና ሌሎች መሰል መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ረቂቅ ሕጎች ስለሚቀርቡበት እና ስለሚመረመሩበት አግባብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የፍትሕ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀፅ 21(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**ለፍትሕ ሚኒስቴር ለምርመራ የሚላኩ ረቂቅ ሕጎች የአቀራረብ እና የምርመራ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር** 910/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ሕገ-መንግሥት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው፤
2) **"ረቂቅ ሕግ"** ማለት በፍትሕ ሚኒስቴር እንዲመረመር ከተቋማት የሚላክ ረቂቅ አዋጅ ወይም ረቂቅ ደንብ ነው፤
3) **"ተቋም"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት የተቋቋመ የፌዴራል መንግሥት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ወይም ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ተጠሪ የሆነ መሥሪያ ቤት ነው፤

4) **"የተቋም የበላይ አመራር"** ማለት የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት የተቋቋመ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሚኒስትር፣ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ተጠሪ የሆነ መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የፍርድ ቤቶች እና ሌሎች ዴሞክራሲ ተቋማት የበላይ አመራር ነው፤

5) **"የረቂቅ ሕግ ምርመራ"** ማለት የአንድን ረቂቅ ሕግ ጥራትና ወጥነት ለማረጋገጥ፣ ከሕግ አረቃቀቅ መርሆዎች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2013 ዓ.ም ከወጣው የሕግ አወጣጥ እና ረቂቅ ሕግ ዝግጅት ማኑዋል፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የአሠራር መመሪያ፣ በፍትሕ ሚኒስቴር በ2014 ዓ.ም የወጣው የሥርዓተ-ፆታ አካታችነት ግምገማ ሀንድቡክ፣ በሥራ ላይ ካሉ ሕጎች፣ ከሕገ-መንግሥቱ፣ ከፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች፣ ከዓለማቀፍ ግዴታዎች አንፃር በመፈተሽ በረቂቁ ላይ የሚታዩ ስህተቶችን የማስተካከል፣ ጉድለቶችን የመሙላት፣ ሌሎች አስፈላጊ ማስተካከያዎችንና ማሻሻያዎችን የማድረግ ሥራ ሲሆን የረቂቁ የይዘት እና የቅርጽ ምልአት መፈተሽን እና ማስተካከል እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ረቂቅ ሕጉን እንደገና ማርቀቅንም ያጠቃልላል፤

6) **"የሚኒስቴሩ የበላይ አመራር"** ማለት የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይም የመንግሥት ሕግና ፍትሕ አገልግሎት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ነው፤

7) **"ሚኒስቴር"** ማለት የፍትሕ ሚኒስቴር ነው፤

8) **"የሥራ ክፍል"** ማለት በሚኒስቴሩ የሕግ ጥናት፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት ጀነራል ነው፤

9) **"የሥራ ክፍል ኃላፊ"** ማለት በፍትሕ ሚኒስቴር የሕግ ጥናት፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዳይሬክተር ጀነራል ወይም ምክትል ዳይሬክተር ጀነራል ነው፤

10) **"የሥራ ክፍሉ ባለሙያ"** ማለት በሕግ ጥናት፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት ጀነራል ውስጥ ረቂቅ ሕግ የማረም ኃላፊነት የተሰጠው ባለሙያ ነው፤

11) **"ማረጋገጥ"** ማለት በረቂቅ ሕግ ላይ አስተያየት የተላከለት ተቋም፣ ረቂቁን በተላከለት አስተያየት መሠረት ያስተካከለው ስለመሆኑ በሚኒስቴሩ በድጋሚ የምርመራ ሥራ መሥራት ማለት ነው፤

## 3. የመመሪያው ዓላማ

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

1) ከመንግሥት ተቋማት ለሚኒስቴሩ ለምርመራ የሚላኩ ረቂቅ ሕጎችን አቀራረብ በሚመለከት ግልፅ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፤

2) ለሚኒስቴሩ ለምርመራ የሕግ ረቂቅ የሚልኩ ተቋማት በረቂቁ ውስጥ ማሟላትና ማካተት ያለባቸውን መስፈርቶች እንዲያውቁ ማድረግ እንዲሁም ረቂቅ ሕጎች ለምርመራ ሲላኩ አብረው መላክ ያለባቸው ሰነዶች ምን ምን እንደሆኑ በግልፅ በመደንገግ የተቋማትን ወጪ እና ጊዜ መቀነስ፤

3) ረቂቅ ሕጎች ለሚኒስቴሩ ለምርመራ ከተላኩ በኋላ በሚኒስቴሩ ውስጥ የሚኖረው ሂደት ምን መሆን እንዳለበት በግልፅ በመደንገግ የአሠራር ሥርዓቱን ገልፅ ማድረግ፣ ረቂቅ ሕጎች ለሚኒስቴሩ ከተላኩ በኋላ የሥራ ክፍሉ ባለሙያዎች በቂ የሆነ ጊዜ ወስደው ረቂቆችን እንዲፈትሹ የሥራ ክፍሉ ኃላፊዎችም የተሰጠውን የባለሙያዎች አስተያየት በዝርዝር በመፈተሽ ደረጃውን የጠበቀ አስተያየት ለተቋማቱ በመላክ የሕጎችን ጥራት ማስጠበቅ፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

መመሪያው ሕግ የማመንጨት ሥልጣን በሕግ ከተሰጣቸው ተቋማት ለሚኒስቴሩ ለምርመራ በሚላኩ ረቂቅ አዋጆች እና ደንቦች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የምርመራ ሥርዓት፣ ለምርመራ የሚላክ ረቂቅ ሕግ አቀባበል ሥርዓት እና ከረቂቁ ጋር አብረው መላክ ያለባቸው ሰነዶች

## 5. የምርመራ ሥርዓት

1) ሚኒስቴሩ ሕግ የማመንጨት ሥልጣን በሕግ ከተሰጣቸው የመንግሥት አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የሚላኩ ረቂቅ ሕጎችን ተቀብሎ አስፈላጊውን ምርመራ ያደርጋል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ የዴሞክራሲ ተቋማት፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ረቂቅ ሕጎችን ለምርመራ የላኩ እንደሆነ የረቂቅ ሕግ ምርመራው ጥያቄ በልዩ ሁኔታ ታይቶ ይስተናገዳል፤

3) ሚኒስቴሩ ለምርመራ የሚላኩ ረቂቅ ሕጎችን የሚቀበለው በላኪው ተቋም የበላይ አመራር በተፈረመ ደብዳቤ አማካኝነት ሲላኩ ብቻ ነው፤

4) ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ተጠሪ ከሆኑ ተቋማት ውጪ ያሉ ለሌሎች ተቋማት ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ረቂቅ ሕጎችን ምርመራ ለሚኒስቴሩ መላክ የሚችሉት ተጠሪ በሆኑላቸው ተቋማት የበላይ አመራር ፊርማ ብቻ ነው፤

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሱት ተቋማት ረቂቅ ሕጎችን ለሚኒስቴሩ ለምርመራ በላኩ ጊዜ ሚኒስቴሩ የሚያደርገው ምርመራ በረቂቁ ውስጥ የተካተቱ ድንጋጌዎች በመንግሥት ተቋማት መካከል ያለውን የእርስ-በርስ የሥልጣን ሚዛን የጠበቁ ስለመሆናቸው፣ ከሕገ-መንግሥቱ፣ ከሌሎች ሕጎች፣ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ከአጠቃላይ የሕግ አረቃቀቅ መርሆዎች አንፃር ችግር የሌለባቸው ስለመሆኑ ላይ ብቻ ያተኮረ ይሆናል፡፡

## 6. ረቂቅ ሕግ ለምርመራ ለሚኒስቴሩ የሚላክበት ሥርዓት

1) ሚኒስቴሩ ለምርመራ የተላከ ረቂቅ ሕግን የሚቀበለው በተቋሙ የበላይ አመራር በተፈረመ ደብዳቤ ሸኚነት በሀርድ ኮፒ እና በሶፍት ኮፒ፣ ወይም፤

2) በተቋሙ የበላይ አመራር በተፈረመ ደብዳቤ ሸኚነት ለሚኒስቴሩ የበላይ አመራሮች ወይም ለሥራ ክፍሉ ኃላፊዎች በሶፍት ኮፒ በኢሜል ወይም በሌላ አስተማማኝ ሰነዶችን የመላኪያ ኤሌክትሮኒክ ዘዴ፤

ሲላክ ብቻ ነው፡፡

## 7. ከረቂቅ ሕጉ ጋር መላክ የሚገባቸው ሰነዶች

የሥራ ክፍሉ ኃላፊ ከማንኛውም ተቋም ለምርመራ ከሚላክ ረቂቅ ሕግ ጋር የሚከተሉት ጉዳዮች መሟላታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡-

1) ከረቂቁ የአማርኛ ቅጂ ጋር የረቂቁ እንግሊዝኛ ቅጂ እና የረቂቁ አጭር ማብራሪያ፤

2) የሚረቀቀው ሕግ እንዲወጣ መነሻ የሆኑ ምክንያቶች፣ ሕጉ ባለመውጣቱ ያጋጠሙ ችግሮች፣ ችግሮቹ ሕግ በማውጣት ብቻ የሚፈቱ ስለመሆናቸው የሚያሳይ የጥናት ሰነድ፤

3) በተቋሙ የበላይ አመራር በተፈረመው ሸኚ ደብዳቤ ላይ ለምርመራ የተላከው ረቂቅ ሕግ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ መርሀ ግብር ውስጥ የተካተተ ወይም በሕግ መርሀ ግብር ውስጥ የተካተተ ባይሆንም ረቂቁ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲቀርብ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ተቀባይነት ያገኙ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

4) በረቂቅ ሕጉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተገቢው ውይይት የተደረገ እና ግብዓት የተሰበሰበ ስለመሆኑ፣ እና

5) ረቂቁ ለተቋሙ የበላይ አመራር በሕግ ክፍሉ በኩል የቀረበ ስለመሆኑ በሸኚ ደብዳቤው ላይ ስለመገለፁ እና የተላኩት ሰነዶች እያንዳንዳቸው ላይ የተፈረመባቸው ስለመሆኑ፡፡

## 8. በረቂቅ ሕግ አጭር ማብራሪያ ውስጥ መካተት የሚገባቸው ነጥቦች

ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚላክ የረቂቅ ሕግ አጭር ማብራሪያ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

1) መግቢያ

2) የሕጉን ማርቀቅ ሂደት በተለይም በረቂቁ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት የተደረገ ስለመሆኑ፣ በውይይቱ ወቅት የተነሱ ዋና ዋና ጉዳዮችና በረቂቁ ውስጥ ስለተካተቱበት አግባብ፣ እንዲሁም በተወያዮች ተነስተው ነገር ግን በረቂቁ ውስጥ ያልተካተቱ ጉዳዮች ጠቅለል ባለ መለኩ እና የልዩነት ሓሳቦች፣

3) ሕጉን ለማውጣት ምክንያት የሆነው መነሻ ችግር፣ ሕጉ ችግሩን እንዴት እንደሚፈታው እና በዚህም ምክንያት የሚመጣ ውጤት ምን እንደሆነ የሚያሳይ የሕጉ መውጣት አስፈላጊነት፤

4) ሕጉን ለማርቀቅ መነሻ የሆነ ፖሊሲ ስለመኖሩ፣ ሕጉ እንዲረቀቅ ትዕዛዝ የሰጠው ማን እንደሆነ፣ የረቂቁን አስፈላጊነት በተመለከተ

የተሠራ ጥናት ስለመኖሩ፣ በጥናቱ ላይ የተደረጉ ምክክሮች፣ በረቂቁ ላይ የተደረጉ ምክክሮች፣ በምክክሩ ወቅት በተነሱ ሓሳቦች ላይ መግባባት ያልተደረሰባቸው ነጥቦች ካሉ፣ የተወሰዱ ዓለምአቀፍ ልምዶች እና መሰል ጉዳዮችን የያዘ የሕጉ የማርቀቅ ሂደት፣

5) ረቂቁ በስንት ምዕራፎች፣ ክፍሎች፣ ንዑስ ክፍሎች እና አንቀጾች እንደተደራጀ እና በእያንዳንዱ ምዕራፍ፣ ክፍል ወይም ንዑስ ክፍል ውስጥ የተካተቱ ዋና ዋና ድንጋጌዎች ምን ምን እንደሆኑ የሚያሳይ የረቂቁ አደረጃጀት፤

6) በረቂቁ ውስጥ በየክፍሎቹ ስለተካተቱት ዋና ዋና ድንጋጌዎች ወይም ለግልፅነት ዓላማ መብራራት የሚገባቸውን ድንጋጌዎች አስመልክቶ አጠር አድርጎ የረቂቁን ይዘት የሚያብራራ፤ እና

7) ማጠቃለያ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ለምርመራ የሚላክ ረቂቅ ሕግን በተመለከተ የሚኒስቴሩ የበላይ አመራር፣ የሥራ ክፍሉ ኃላፊ እና የሥራ ክፍሉ ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

### 9. የሚኒስቴሩ የበላይ አመራር ተግባርና ኃላፊነት

ለምርመራ የሚላኩ ረቂቅ ሕጎችን በተመለከተ የሚኒስቴሩ የበላይ አመራር የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1) ከተቋማት በሀርድ ኮፒ፣ በሶፍት ኮፒ በኢሜይል ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለምርመራ የተላኩ ረቂቆችን በተቻለ ፍጥነት ለሥራ ክፍሉ የመላክ፤

2) የተቋማት የበላይ አመራሮች ለምርመራ የተላኩ ረቂቅ ሕጎች ላይ በአስቸኳይ አስተያየት እንዲሰጣቸው በሚጠይቁበት ጊዜ፣ በተቋሙ ስላለው የሕግ ምርመራ ሥርዓት መረጃ የመስጠት እና ረቂቅ ሕጎች ጊዜያቸውን ጠብቀው በጥንቃቄ ምርመራ እንዲደረግባቸው ለሥራ ክፍሉ ድጋፍ የማድረግ፤

3) የተለየ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ረቂቅ ሕጎች ላይ የሚሰጡ አስተያየቶችን በተመለከተ በራሳቸው ወይም በሥራ ክፍሉ አነሳሽነት ከሥራ ክፍሉ ጋር በጋራ መወያየት እና የተሰጡ አስተያየቶችን በተመለከተ አቅጣጫ ማስቀመጥ፤

4) ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በአጀንዳነት የቀረቡ ረቂቅ ሕጎች ላይ በሥራ ክፍሉ የመጨረሻ ምርመራ እንዲደረግባቸው የማድረግ፡፡

### 10. የሥራ ክፍሉ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

የረቂቅ ሕግ ምርመራ ሥራን በተመለከተ የሥራ ክፍሉ ኃላፊ፡-

1) ለምርመራ የሚላኩ ረቂቅ ሕጎች ለባለሙያዎች የሚመሩበትን ሥርዓት የመዘርጋት፣ ለባለሙያዎች የሚመሩ ረቂቅ ሕጎችን መከታተያ ቅፅ የማዘጋጀትና በዚያው አግባብ ሥራውን የመከታተል ኃላፊነት አለበት፤

2) የሕግ ምርመራ ሥራ የሚሠሩ የሥራ ክፍሉ ባለሙያዎች አስተያየት ሊሰጡ የሚችሉባቸውን የሕግ ዓይነቶች፣ የትምህርት ዝግጅት፣ የወሰዱትን የሥልጠና ዓይነት፣ በተለያዩ የሕግ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ፣ ረቂቁ ሲዘጋጅ የነበራቸውን ተሳትፎ ወይም የሕግ ዝንባሌያቸውን የመለየትና መረጃ መያዝ እንዲሁም ረቂቆቹ ለምርመራ ሲላኩ በዚያው አግባብ ቀረቤታ ላለው ባለሙያ የመምራት ኃላፊነት አለበት፤

3) ለሥራ ክፍሉ ለምርመራ የሚላኩ ረቂቅ ሕጎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6፣ 7 እና 8 በተገለጸው አግባብ የተላኩ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣ እነዚህ ሥርዓቶችና ሰነዶች ያልተሟሉ ከሆነ ለላኪው ተቋም የጎደሉትን እንዲያሟሉ የመንገር፣ በቀላሉ አይሟሉም ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ ችግሮቹን በመግለጽ ለላኪው ተቋም ችግሮቹን አስተካክሎ እንዲልክ በደብዳቤ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት፤

4) ረቂቅ ሕጎች ለምርመራ ሲላኩ በአንድ ሰው ወይም በቡድን የሚሠሩ ስለመሆን አለመሆናቸው የመለየት እና በዚያው አግባብ ለባለሙያ ወይም ለባለሙያዎች የመምራት፣ ባለሙያዎቹም በቂ ጊዜ ወስደው እንዲሠሩ የማድረግ ኃለፊነት አለበት፤

5) አንዳንድ አስቸኳይ ወይም ልዩ ትኩረት የሚሹ ረቂቅ ሕጎችን ራሱ መመርመር ይችላል፤

6) ለምርመራ የተላከው ረቂቅ ሕግ መሠረታዊ የሕግ ቅርፅ ያልያዘ ከሆነ ወይም ሌላ መሠረታዊ ግድፈት ያለበት መሆኑን ከተረዳ ረቂቁን ለባለሙያ ከመምራት ይልቅ እንደገና ተስተካክሎ እንዲመጣ ረቂቁን ለላከው ተቋም ረቂቁ ላይ የተስተዋለውን ችግር በመግለፅ ችግሮቹን አስተካክሎ እንዲልክ በደብዳቤ የመግለፅ ኃላፊነት አለበት፤

7) ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ምርመራ የሚደረግባቸው ረቂቅ ሕጎች በቡድን እንዲታዩ ማድረግ የሚችል ሲሆን፣ ውስብስብ የሆኑ ጉዳዮችን የያዘ ረቂቅ ሕግ ግን ሁልጊዜም በቡድን እንዲመረመር የማድረግ ግዴታ አለበት፤

8) ለምርመራ የመጡ ረቂቅ ሕጎችና ተያያዥ ሰነዶች እንዲሁም የተሰጡ አስተያየቶች በሀርድ ኮፒ እና በሶፍት ኮፒ ተደራጅተው የሚቀመጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፤

9) በሥራ ክፍሉ ባለሙያ የተደረጉ የረቂቅ ሕግ ምርመራዎችን ለሚመለከተው አካል ከመላኩ በፊት በተቻለ መጠን በዝርዝር ማየት ይኖርበታል፣ ከአቅሙ በላይ የሆኑ ጉዳዮች ካሉም ከበላይ አመራሩ ጋር በመነጋገር አቅጣጫ እንዲሰጠው ያደርጋል፤

10) ምርመራ ለተደረገባቸው ረቂቅ ሕጎች የይሁንታ ደብዳቤ ይጽፋል፤

11) በዚህ አንቀጽ መሠረት በተደረገው ምርመራ ላይ በላኪ ተቋሙ እና በሥራ ክፍሉ መካከል ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ፡-

ሀ/ የልዩነት ሓሳቡ ከሕግ ማርቀቅ ቴክኒኮች፣ ከሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች፣ ከነባር ሕጎች ወይም መሰል ጉዳዮች ጋር የተገናኘ ከሆነ ላኪው ተቋም እንዲቀበል እና እንዲያስተካክል ይደረጋል፤

ለ/ የልዩነት ሓሳቡ ከላይ በ /ሀ/ ላይ ከተመለከቱት ጉዳዮች ውጪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከሆነ የልዩነት ሓሳቡ በማብራሪያው ላይ እንዲገለፅ በማድረግ እና ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ እንዲሰጥበት በማሳሰብ ማረጋገጫ ደብዳቤውን ይጽፋል፤

ሐ/ በዚህ አንቀጽ የንዑስ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከላኪው ተቋም የመጣው ሕግ ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ እና የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቅ ሆኖ ነገር መሠረታዊ የሆነ የአረቃቀቅ ችግር ያለበት በሆነ ጊዜ የሥራ ክፍሉ ረቂቁን አስተካክሎ በማርቀቅ በላኪው ተቋም በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲላክ ሊያደርግ ይችላል፤

## 11. ረቂቅ ሕግ ለምርመራ የተመራለት የሥራ ክፍሉ ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

በረቂቅ ሕግ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ በሥራ ክፍሉ ኃላፊ የተመራለት ባለሙያ፡-

1) የተመራለት ረቂቅ ሕግ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6፣ 7 እና 8 በተገለጸው አግባብ የተላከ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ያልተሟሉ ነገሮች በሚኖሩበት ጊዜ ስለሁኔታው ለሥራ ክፍሉ ኃላፊ ያሳውቃል ወይም ከላኪው ተቋም የሕግ ክፍል ጋር በቀጥታ በመገናኘት የጎደሉ ነገሮች እንዲላኩለት ሊጠይቅ ይችላል፤

2) የተመሩለትን ረቂቅ ሕጎችና ተያያዥ ሰነዶች በጥንቃቄ መያዝ አለበት፤

3) የተመራለትን ረቂቅ ሕግ የሥራ ክፍሉ ባዘጋጀው መረጃ መያዣ ሥርዓት መሠረት ይመዘግባል፤

4) አስተያየት መጻፍ ከመጀመሩ በፊት በረቂቅ ሕጉ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ግንዛቤ ለማግኘት አስፈላጊ ሰነዶችን በማንበብ፣ ዓለምአቀፍ ልምዶችን በማየት እና ከነባር ባለሙያዎች በመጠየቅ ስለጉዳዩ ለመረዳት ጥረት ማድረግ አለበት፤

5) ለምርመራ የተመራለትን ረቂቅ ሕግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ አጠናቆ የምርመራ ሥራውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለኃላፊው ማቅረብ ይኖርበታል፤

6) ባለሙያው ምርመራ በሚያደርግበት ጊዜ፡-

ሀ) ሊስተካከል የሚገባው ጉዳይ ወይም ነገር እንዴት መታረም እንዳለበት በማሳየትና እንዲስተካከል የላከው አካልም ይህንኑ እንዲያደርግ መግለጽ ይኖርበታል፤

ለ) የሚያደርገውም ማስተካከያ አስተያየታዊ ሳይሆን አረጋጋጭ በሆኑ ቃላት መገለጽ ይኖርበታል፤

ሐ) እንዲስተካከል የተፈለገው አንድ ሓሳብ በደፈናው ይስተካከል ከማለት ወይም እንዲህ ቢሆን ወይም ቢደረግ የሚል ሓሳብ ከማቅረብ ወይም ጥያቄ በመጠየቅ ከመግለጽ ይልቅ የሚስተካከለውን ነገር በመግለጽ "እንዲህ ይስተካከል፣ ይደረግ" በሚሉ አረጋጋጭ ቃላት መግለጽ አለበት፣

7) ባለሙያው ረቂቅ ሕጎቹን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ውጭ ለማንም ሰው መረጃ መስጠት ወይም የረቂቆቹን ምስጢራዊነት ማጋለጥ የለበትም፡፡

## ክፍል አራት

## ምርመራ የሚደረግበት የአሠራር ሥርዓት

12.በረቂቅ ሕግ ይዘት ላይ ምርመራ

በረቂቅ ሕግ ላይ ምርመራ የሚያደርግ የሥራ ክፍሉ ባለሙያ የሚከተሉትን መሠረታዊ የይዘት ጉዳዮች ማየት ይኖርበታል፡-

1) ረቂቅ ሕጉን አዘጋጅቶ የላከው ተቋም ረቂቅ ሕጉን የማመንጨት ሥልጣንና አግባብ የሆነ የሕግ መሠረት ያለው እንዲሁም ረቂቅ ሕጉ እንዲገዛው የተፈለገው ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ ስለመሆኑ፤

ይህም ሲባል፡-

ሀ) ሕጉን ያረቀቀው ተቋም ረቂቅ ሕጉን ለማመንጨት በሕግ ሥልጣን ስለመሰጠቱ፤

ለ) የሚወጣው ሕግ ደንብ በሆነ ጊዜ ደንቡ እንዲወጣ ስልጣን የሚሰጥ እናት ሕግ ወይም አስቻይ ሕግ ስለመኖሩ፤

ሐ) በረቂቅ ሕጉ ውስጥ የተካተተው ጉዳይ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 51 እና 52 መሰረት የረቂቅ ሕጉ ይዘት የፌዴራል ጉዳይ ስለመሆኑ፤

2) ሕግ የማውጣት ሥልጣን ሲጠቀስ የዚሁ ሥልጣን ምንጭ የሆነው ቀጥተኛ እናት ሕግ መገለጹ ብቻ በቂ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ረቂቅ ሕጉ ከሀገሪቱ ሕገ-መንግስት፣ የሕገ-መንግስቱ መሠረታዊ መርሆዎችና ከፌዴራል ሥርዓቱ አወቃቀር ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ፤

3) ረቂቅ ሕጉ ሰብዓዊ መብቶችንና ነጻነቶችን የማይጻረርና ለፍርድ ቤት ተደራሽ የመሆን መብትን የማይከለክል ስለመሆኑ፤

4) ረቂቅ ሕጉ የሴቶች፣ የሕጻናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋዊያን መብቶችን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባና ያከበረ መሆኑን ማረጋገጥ፤

5) ሕጉን ለማርቀቅ በተሰራው ጥናት እና በረቂቁ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተገቢ ውይይት ስለመደረጉ እና የተገኙ ግብአቶችም በረቂቁ የተካተቱ ስለመሆኑ፣

6) ረቂቅ ሕጉ ከፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና በሥራ ላይ ካሉ በእኩል ደረጃ ወይም የበላዩ ሕግ ጋር የተጣጣመና የማይጣረስ ስለመሆኑ ወይም እኩል ደረጃ ጋር ያለውን ማሻሻል ሲፈለግ ይኸው የተገለጸ ስለመሆኑ፤

ይህ ሲባል፡-

ሀ) ለረቂቅ ሕጉ መነሻ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ማስፈጸሚያ የሆኑ ስትራቴጂዎች ከረቂቁ ጋር መጣጣማቸውን መረጋገጥ አለበት፤

ለ) የሚረቀቀው ሕግ አዋጅ ከሆነ በሥራ ላይ ካሉ ሌሎች አዋጆች ጋር የማይቃረን መሆኑን ወይም የሚቃረን ይዘት ካለው በሥራ ላይ ያለው ሕግ በግልጽ ጠቅሶ መሻር አለበት፤

ሐ) የሚረቀቀው ሕግ ደንብ ከሆነ ከበላይ ያለውን አዋጅ መቃረን የለበትም፤ ሆኖም ግን በእኩል ደረጃ ላይ ከሆኑ በግልጽ ጠቅሶ መሻር አለበት፤

7) በረቂቅ ሕጉ የተካተተው ጉዳይ ከዚህ በፊት በነበሩ ሕጎች የተሸፈነ ወይም የተገለጸ አለመሆኑን ማረጋገጥ፤

8) ረቂቅ ሕጉ በሕግ ይረቀቅልኝ መመሪያ ውስጥ የተቀመጠውን ዓላማ ማሳካት የሚችል መሆኑን እንዲሁም የረቂቁ መግቢያ እና ዓላማ ሊይዛቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መያዙን እና በረቂቅ ሕጉ የተካተተውን ሀሳብ በሚገባ የሚገልጽ መሆኑን ማረጋገጥ፤

9) በሕጉ ውስጥ የሚጠቀሱ ማናቸውም ተቋማት ስም በትክክልና በአግባቡ መጠቀሱን ማረጋገጥ፣ ስያሜያቸው የተሻሻሉ ወይም የተቀየሩ ተቋማት በየጊዜው ክትትል በማድረግ በተስተካከለው አዲሱ ስያሜ መጠቀም ይኖርባቸዋል፤

10) በረቂቅ ሕጉ ላይ የተካተተው ርዕሰ-ጉዳይ ከሚረቀቀው ሕግ ተዋረዳዊ ደረጃ ጋር አግባብነት ያለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ላይ የሚደነገግ ጉዳይ በደንብ ላይ አለማካተቱን፤

11) የረቂቅ ሕጉ ዓላማ የእናት ሕጉን ለማስፈጸም በሚሆንበት ጊዜ የእናት ሕጉን ድንጋጌዎች የማይደግም፣ ወሰን የማያልፍ እና ለማስፈጸም የሚያመች መሆኑን ማረጋገጥ፣ ይህም ማለት የሚወጣው ደንብ ከሆነ የአዋጁን ወሰን የጠበቀና የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል፤

12) ረቂቅ ሕጉ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 9(4) መሠረት የሀገሪቱ ሕጎች አካል ስለሆኑ ከእነዚህ ስምምነቶች ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል፤

13) ረቂቅ ሕጉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ለማስፈጸም ከሆነ የስምምነቱን ዓላማ በሚገባ ያገናዘበ እና ያለመግባባትን ለመፍታት በስምምነቱ ከተዘረጋው ሥርዓት ጋር የተጣጣመ እንዲሁም በስምምነቱ ላይ ሀገሪቱ ያቀረበችው የልዩነት ሀሳብ ካለ ይኸው ስለመኖሩ ታይቶ ማስተካከያ እርማት መሰጠት ይኖርበታል፤

14) በረቂቅ ሕጉ ውስጥ ቀደም ብሎ በነበረው ሁኔታ፣ መብትና ግዴታ ላይ ወደ ኋላ ተመልሶ ተጽዕኖ አለማድረጉን፤ ረቂቅ ሕጉ በተለየ ሁኔታ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሠራ ከታሰበ ቀድመው የነበሩት መብቶች፣ ግዴታዎች እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ተጽዕኖ አለማድረጉን እንዲሁም በፍርድ ሂደት ያገኙትን መብት ወይም ቀደም ብሎ በነበረ ሕግ መሠረት መብት እንዳይጠይቁ የሚከለክል አለመሆኑን፤

15) በረቂቅ ሕጉ የትርጓሜ ክፍል ውስጥ፡-

ሀ) ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረጎች ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ስለመሆኑ፣

ለ) ዙሪያ ጥምጥም ትርጉም አለመሆኑን፤

ሐ) ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች በረቂቁ ድንጋጌዎች ውስጥ በተተረጎሙበት አግባብ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው፣

መረጋገጥ አለበት፤

16) በረቂቅ ሕጉ የተካተቱ ጉዳዮች የመሸጋገሪያ እና የማቆያ ድንጋጌዎች የሚያስፈልጉ ከሆነ እነዚሁ መካተታቸው ማረጋገጥ፣

ሀ) የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ረቂቅ ሕጉ ያካተታቸው አንዳንድ ጉዳዮች አዲሱ ሕግ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ወዲያውኑ ለመፈጸም የማይቻል ሲሆን ነባሩ ሕግ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆንበት ነው፤

ለ) የማቆያ ድንጋጌ በነባሩ ሕግ ላይ የተወሰዱት እርምጃዎች፣ አቅጣጫዎች ወይም ትዕዛዞች በአዲሱ ሕግ ላይ እንዲቀጥሉ የሚያደርግ ድንጋጌ ነው፤

17) ረቂቅ ሕጉ ለሚያስቀምጠው እያንዳንዱ ግዴታ ማስፈጸሚያ፡-

ሀ) ተገቢ የሆነ የወንጀል፣ የፍትሐ-ብሔር እና አስተዳደራዊ ስልቶች ስለማስቀመጡ፤

ለ) የተቀመጠው የወንጀል ድንጋጌ ቅጣት ከሆነ በተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የማስረዳት ሸክም የዐቃቤ ሕግ ስለመሆኑ፤

መረጋገጥ አለበት፤

18) ረቂቅ ሕጉ አንድ የወንጀል ድርጊት ተፈጸመ ለማለት የሚያስችሉ የሀሳብ፤ የድርጊት እና የሕግ ክፍሎች ግልጽ በሆነ ሁኔታ ማስቀመጡን መረጋገጥ ይኖርበታል፤

19) በሚወጡ ደንቦች፤

20) በአስተዳደር ወይም በፍትሐብሔር እርምጃ ማስፈጸም የሚቻለውን ጉዳዮች ላይ የወንጀል ቅጣት አለመጣሉን፤

21) በረቂቁ ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም ድንጋጌዎች መጣስ በወንጀል ያስቀጣል በማለት መደንገግ የሌለበት በመሆኑ ይህ አለመሆኑን የማረጋገጥ፤

22) የሚወሰደው የፍትሐብሔር ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ ለተፈጸመው ጥፋት ወይም ጥሰት የተመጣጠነ፣ ምክንያታዊ እና አስተማሪ ስለመሆኑ ማረጋገጥ፤

23) በረቂቅ ሕጉ ላይ የተቀመጠውን መብት፣ ግዴታና ሌሎች እርምጃዎችን ለማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጣቸው አስፈጻሚ አካላት ተለይተው በግልጽ መቀመጣቸውን እንዲሁም እነዚህ አካላት እርምጃውን ለማስፈጸም አግባብነት ያለው ሥልጣን ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤

## ክፍል አምስት
## ድጋሚ ምርመራ የሚደረግበት ሥርዓት

### 13.የተሰጡ አስተያየቶችን ስለማካተት እና የልዩነት ሓሳቦችን ስለማቅረብ

1) በረቂቅ ሕግ ላይ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስተያየት የተላከለት ተቋም፣ የተሰጡትን አስተያየቶች በሙሉ የተቀበላቸው እንደሆነ፣ በዚያው አግባብ አስተካክሎ ለሚኒስቴሩ በድጋሚ በመላክ፣ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ረቂቁን መላክ እንዲችል የማረጋገጫ ደብዳቤ እንዲፃፍለት መጠየቅ ይችላል፤

2) የሥራ ክፍሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት ረቂቁ በተሰጠው አስተያየት መሠረት መስተካከሉን በማረጋገጥ፣ ደብዳቤውን በሦስት ቀናት ውስጥ የመፃፍ ኃላፊነት አለበት፤

3) በቀረበው ረቂቅ ሕግ ላይ አስተያየት የተላከለት ተቋም በተሰጠው አስተያየት መሠረት አስተያየቱን በረቂቁ ውስጥ ካካተተ በኋላ፣ ያልተስማማበት ነጥብ ካለ ይህንኑ ለብቻው ለይቶ በመፃፍ ለሥራ ክፍሉ በማንኛውም ሰዓት በማቅረብ ውይይት እንዲደረግበት መጠየቅ ይችላል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ጥያቄ በቀረበ ጊዜ የሥራ ክፍሉ ኃላፊ እና አስተያየቱን ያዘጋጁት የሥራ ክፍሉ ባለሙያዎች ጥያቄውን ካቀረበው ተቋም የሚመለከተው ኃላፊ እና ረቂቁን በማዘጋጀት ከተሳተፉ ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር ጉዳዩ በቀረበ በአምስት ቀናት ውስጥ ለጉዳዩ እልባት መሰጠት አለበት፤

5) የሥራ ክፍሉ ኃላፊ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ካልተስተካከለ፣ ወይም የልዩነት ሓሳብ የተፈጠረው መሠረታዊ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ከሆነ ይህንኑ በማብራሪያው ላይ እንዲገለፅ በማድረግ እና ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ እንዲሰጥበት በማሳሰብ የመጨረሻ ውይይት ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ 3 (ሦስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የይሁንታ ደብዳቤውን አዘጋጅቶ ይልካል፤

6) የሥራ ክፍሉ ኃላፊ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ያልተስተካከለ ወይም የልዩነት ሓሳቡ መሠረታዊ የሕግ፣ የሕገ-መንግሥት እና የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ከሆነ በዚያው አግባብ እንዲስተካከል ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. የሌሎች ሰነዶች ተፈፃሚነት

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣው የሕግ አወጣጥ እና የረቂቅ ሕግ ዝግጅት ማኑዋል፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአሠራር መመሪያ እና በፍትሕ ሚኒስቴር የተዘጋጀው በሕግ ማርቀቅና አተገባበር ሂደት የሥርዓተ-ፆታ አካታችነት ግምገማ ሀንድቡክ የዚህ መመሪያ አካል ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡

### 15. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሠራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### 16. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ዕለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ ሰኔ 14 ቀን 2014 ዓ/ም**

ጌዲዮን ጢሞቲዮስ (ዶ/ር)

ሚኒስትር